# ለልጅዎ የጆሮ ህክምና (ኦዲዮሎጂ) ቀጠሮ መዘጋጀት

የሚኒሶታ አራስ ህጻናት
የምርመራ ፕሮግራም

**የልጅዎ የጆሮ ህክምና (ኦዲዮሎጂ) ቀጠሮ**

| | |
|---|---|
| ቀን (ወር/ቀን/አመት)፦ | |
| ሰአት (ከሰኣት በፍት/ከሰኣት በኃላ)፦ | |
| የክሊኒክ ስም፦ | |
| የክሊኒክ ስልክ፦ | |

## የጆሮ ህክምና ባለሙያ ምንድን ነው?

የጆሮ ህክምና ባለሙያ በአራስ ህጻናት፣ ልጆች እና አዋቂዎች የሚከሰት የመስማት እክል ለመመርመር እና ለማከም የሰለጠነ የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ነው። የመስማት እክል ያለበት ሰው የተወሰኑ ድምጾችን መስማት የሚችል ሲሆን ሌሎች ደግሞ ምንም መስማት የማይችሉ ናቸዉ። በአንድ ወይም በሌሎች ጆሮ(ዎች) ክፍሎች ላይ በሚገኘው ልዩ ችግር ላይ በመመስረት የተለያዩ የመስማት እክል አይነቶች ይኖራሉ። ልምድ ባለው የህጻናት የጆሮ ህክምና ባለሙያ የሚደረግ የጆሮ እክል አይነትም ሆነ ክብደት የተሟላ ግምገማ የመስማት እክልን ለመከታተል እና ለማከም እና የመሰማት እክልን ለመቆጣጠርይበልጥ ትክክለኛ የሆነ እቅድ መውጣቱን ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

## ልጄ የጆሮ ህክምና ባለሙያን እየጎበኘ ያለው ለምንድን ነው?

ልጅዎ ሲወለድ/ከተወለደ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያጋጠመዉ የመስማት ችሎታ ምርመራ የማጣሪያ ምርመራ ነበር። ህጻኑ የማጣሪያ ምርመራውን ካላለፈ፣ በጆሮ ህክምና ባለሙያ ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ይነግረናል። ልጅዎ ለንግግር እና ለቋንቋ እድገት አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉንም ድምጾች እየሰማ እንደሆነ በእርግጠኝነት ማወቅ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ በጆሮ ህክምና ባለሙያ በሚደረግ የተሟላ ግምገማ ነው።

## ቀጠሮው ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?

ቀጠሮዎች ከ1-3 ሰአታት ሊወስዱ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ የመስማት ችሎታ ምርመራን ሁል ጊዜ በአንድ ቀጠሮ መጨረስ አይቻል ይሆናል። ሁለተኛ ቀጠሮ ካስፈለገ በተቻለ ፍጥነት ቀጠሮ የሚያዝ ይሆናል።

## ወደ ልጄ ቀጠሮ ስመጣ ምን ይዤ መምጣት አለብኝ?

- የመድን ካርድዎን
- አስፈላጊ ከሆነ ሪፈራል
- በአሁን ጊዜ እየተወሰዱያሉ መድሃኒቶች ዝርዝር
- ከዚህ ቀደም የተደረጉ የመስማት ችሎታ ምርመራ ውጤቶች እና/ወይም ግምገማዎች
- የልጅነት የመስማት ችግር ስላጋጠመው ማንኛውም የቤተሰብ ታሪክ ዝርዝሮች
- ሪፖርቱ እንዲላክላቸው የሚፈልጓቸው ግለሰቦች ስሞች/አድራሻዎች

## ከቀጠሮው በፊት ምን ማድረግ ይኖርብኛል?

ምርመራዎቹ በጣም በቀላሉ ሊከናወኑ የሚችሉት ልጅዎ በሚተኛበት ጊዜ ነው። በምርመራው ወቅት ልጅዎ መተኛቱን ለማረጋገጥ፦

- ከቀጠሮው በፊት ወይም ወደ ክሊኒኩ በመኪናዎ በሚመጡበት ጊዜ ልጅዎ እንዲያሸልብ አይፍቀዱ።
- ከቀጠሮው በፊት ልጆዎን ከመመገብ ይቆጠቡ። ምርመራው ከመደረጉ በፊት ልጅዎን በክሊኒኩ ውስጥ መመገብ ይችላሉ።



## በጆሮ ህክምና (ኦዲዮሎጂ) ቀጠሮ ወቅት ምን ሊከሰት ይችላል?

የጆሮ ህክምና ባለሙያ ስለ ልጅዎ የህክምና ታሪክ፣ ስለዚህ ልጅ እርግዝና/ምጥ/ዉልደት እና ስለ ቤተሰብ ታሪክ መረጃ ይወስዳል።

ልጅዎ በሚተኛበት ጊዜ፣ የጆሮ ህክምና ባለሙያው የልጅዎን ጆሮዎች የሚመረምር ሲሆን የመስማት ችሎታ ግምገማ ያካሂዳል። የተከናወነውን የምርመራ አይነትሊያካትት የሚችለው፡-

- Auditory Brainstem Response (ABR) – አንጎል ለድምጾች የሚሰጠውን ምላሽ ለመለካት ቃኚ መሳሪያዎች በልጅዎ ግንባር እና በጆሮ ቅጠል ላይ የሚቀመጡ ይሆናል። የምርመራ ድምጾችን ለማድረስ የጆሮ ማዳመጫዎች በእያንዳንዱ ጆሮ ላይ የሚቀመጡ ይሆናል። ልጅዎ ለድምጾቹ አካላዊ ምላሽ አይሰጥም፣ ነገር ግን ቃኚ መሳሪያዎቹ ልጅዎ ለተለያዩ ድምጾች ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ ምላሽ እየሰጠ እንደሆነ መለካት ይችላሉ። ይህ ምርመራ ማንኛውም የመስማት እክል ካለ ለማወቅ ይረዳል። የመስማት እክል ካለ፣ ምን አይነት የመስማት እክል እንደሆነ መረጃ መስጠት ይችላል።
- Otoacoustic Emissions (OAE) – ለስላሳ ድምጾች ለማድረስ እና ጆሮው አብዛኛውን ጊዜ በሚሰራበት ጊዜ የሚከሰተውን ማስተጋበት ለመለካት ለስላሳ የፕላስቲክ ጫፍ በእያዳንዱ ጆሮ ላይ የሚደረግ ይሆናል። ይበልጥ ትክክለኛ የሆነ ምርመራ ለማድረግ አብዛኛውን ጊዜ ይህ ምርመራ ከሌሎች ምርመራዎች ጋር በጥምረት ጥቅም ላይ ይውላል።
- Tympanometry – የጆሮ ታምቡር ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ እንደሚንቀሳቀስ የሚለካ ለስላሳ የፕላስቲክ ጫፍ በእያንዳንዱ ጆሮ ላይ ይደረጋል። ይህ ምርመራ፣ ከሌሎች ሙከራዎች ጋር በጥምረት ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ የመስማት እክሉ ሊከሰት የቻለበትን ምክንያት የተወሰኑ ፍንጮችን ሊሰጥ ይችላል።

## ልጄ የህመም ስሜት ይሰማዋል?

ምርመራው በሚደረግበት ወቅት ልጅዎ በማንኛውም ጊዜ ምንም አይነት ህመም አይሰማውም። ለስላሳ የፕላስቲክ ጫፎች እና የቃኚ መሳሪያዎች አቀማመጥ ልጅዎን አይጎዱም። የምርመራ መሳሪያው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀመጥ አብዛኛዎቹ ህጻናት ይረበሻሉ እንዲሁም ይቁነጠነጣሉ ነገር ግን ወደ ራሱዎ ሲያስጠጉ እና ሲታቀፉ ይረጋጋሉ።



## የምርመራውን ውጤቶች ወዲያውኑ አገኛለሁ?

የጆሮ ህክምና ባለሙያው የምርመራ ውጤቶቹ ማግኘት የሚቻልበትን ጊዜ እና ውጤቶቹን ማን እንደሚሰጥዎት ሊነግሩዎት ይችላሉ። ስለ ውጤቶቹ ጥያቄዎች ካሉ፣ የጆሮ ህክምና (ኦዲዮሎጂ) ክሊኒኩን ሊያነጋግሩ ይገባል።

## ልጄ በምርመራው ወቅት ካልተኛስ?

ልጅዎ ጨቅላ በሆነ ቁጥር፣ በምርመራው ወቅት የመተኛት እድላቸው ከፍ ያለ ነው፣ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ተጨማሪ ቀጠሮ ያስፈልጋል። ለአንዳንድ ትልልቅ ህጻናት የተሟላ ግምገማ ለማድረግ በሚያስፈልገው ጊዜ ሁሉ እንዲተኙ ለማገዝ የልጅዎ ሃኪም ማደንዘዣ ሊመከር ይችላል። ማደንዘዣ የመውሰድ እድልን ለመቀነስ፣ በተቻለ ፍጥነት ቀጠሮዎችን እንዲያደርጉ ይመከራል።

## የሆነ ነገር ቢከሰት፣ እና የልጄን ቀጠሮ ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ቢኖርብኝስ?

ልጅዎ የጆሮ ህክምና ባለሙያን መጎብኘቱ በጣም ወሳኝ ነው። መርሃ ግብር በተያዘለት ቀጠሮ መገኘት ካልቻሉ፣ እባክዎ የመስማት ችሎታ ምርመራውን ወዲያውኑ ለሌላ ጊዜ ያስተላልፉ።

DEPARTMENT OF HEALTH
Minnesota Newborn Screening Program | www.health.state.mn.us/newbornscreening
P.O. Box 64899, St. Paul, MN 55164
ይህንን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት፡- ን ያነጋግሩ
ወይም በ (800) 664-7772 ይደውሉ *አስተርጓሚዎች ተዘጋጅተዋል
የተሻሻለው 05/2024
መታወቂያ# 56451